ሌ እርስዋም፡ እንደ፡ ተገለጠላ
ቱ፡ በሰሙ፡ ጊዜ፡ አላመኑዋትም
፲፪ ከዚያ፡ በኋላ፡ ከእነርሳቸው፡ ለ
ሁለቱ፡ ወደ፡ እግር፡ ሲሔዱ፡ በ
መንገድ፡ በሌላ፡ መልክ፡ ተገለ
ጠ። ሉቃ፡ ፳፬፡ ፲፫፡ ፴፭።
፲፫ እርሳቸውም፡ ሔደው፡ ለባልን
ጀሮቻቸው፡ ነገሯቸው፡ እነዚ
ያንም፡ ደግሞ፡ አላመኗቸው
፲፬ ም። በኋላም፡ ለአሥራ፡ አንዱ፡ ተ
ቀምጠው፡ ሲበሉ፡ ተገለጠ፡ ስለ
ሃይማኖታቸውም፡ መጉደልና
ስለ፡ ልባቸውም፡ ድንቁርና፡ ገሠፃ
ቸው፡ እነዚያ፡ ተነሥቶ፡ ያዩ ት
፲፭ ን፡ አላመኗቸውምና። ዓላቸው
ም፡ ወደ፡ ዓለም፡ ሁሉ፡ ሒዳችሁ፡
ለፍጥረቱ፡ ሁሉ፡ ወንጌልን፡ ስበ
ኩ። ማቴ፡ ፳፰፡ ፲፰፡ ፲፱።
፲፮ ያመነም፡ የተጠመቀም፡ ይድና
ል። ያላመነ፡ ግን፡ ይፈረድበታል
የሐዋ፡ ፪፡ ፴፰።
፲፯ ያመኑትን፡ ግን፡ ይህች፡ ተአምራ
ት፡ ትከተላቸዋለች፡ በስሜም፡ ሰ
ይጣናትን፡ ያወጣሉ፡ በሌላም፡ ሐ
ዲስ፡ ቋንቋ፡ ይናገራሉ። የሐ፡ ፪፡ ፬
፲፰ ፲፩፡ ፲፡ ፵፮፡ ፲፱፡ ፮። እባቦችንም፡
ይይዛሉ፡ የሚገድልም፡ ነገር፡ መ
ርዝ፡ ቢጠጡ፡ አይጎዳቸውም፡
እጆቻቸውንም፡ በድውያን፡ ላይ፡ ይ
ጭናሉ፡ እነርሳቸውም፡ ይድናሉ
ሉቃ፡ ፲፡ ፲፱፡ የሐዋ፡ ፳፰፡ ፫፡ ያዕ፡ ፭፡ ፲፬
፲፱ ፲፭። ጌታችንም፡ ከተናገራቸው
በኋላ፡ ወደ፡ ሰማይ፡ ዐረገ፡ በአባ
ቱም፡ በእግዚአብሔር፡ ቀኝ፡ ተ
ቀመጠ። የሐዋ፡ ፩፡ ፩፡ ፲፩።
፳ እነርሳቸውም፡ ወጥተው፡ በስፍ
ራው፡ ሁሉ፡ ሰበኩ፡ ጌታም፡ ይረዳቸ
ው፡ ነበረ። ቃሉንም፡ በምልክት፡ ከተሉ
ተአምራት፡ ያጸና፡ ነበረ፡ (አሜ
ን። ዕብ፡ ፪፡ ፬።

የማርቆስ፡ ወንጌል፡ ተፈጸመ።